# ነፍሰጡር ኖት? እራሶዎን እና ልጅዎን ከፐርቱሲስ ይጠብቁ



## ፐርቱሲስ (“ትክትክ ሳል”)፡ ለሕፃናቶች አደገኛ በሽታ

- በዋሽንግተን ውስጥ እና በአገር አቀፍ ወስጥ የፐርቱሲስ የቅርብ ወረርሽኝ በታዳጊ ሕፃናት ላይ ወደ ሆስፒታል መግባት እና ሞትን አስከትሏል።
- ከፐርቱሲስ ከአንድ አመት በታች የሚገኙ ሕፃናት ለሆስፒታል መግባት እና ለሞት ለከፍተኛ አደጋ ተጋልጠዋል፤ የ 2ወር ሕፃናት እና ከዛ በታች ያሉ ከፍተኛ አደጋ ላይ ናቸው።
- ፐርቱሲስ በማሳል እና በማስነጠስ በቀላሉ የሚተላለፍ በሽታ ነው።
- በሕፃናቶች ላይ፣ ፐርቱሲስ ኑሞኒያ፣ መራድ፣ የአምዕሮ መጎዳት፣ እና ሞት ሊያስከትል ይችላል። ባደጉ ሕፃት ላይ እና አዋቂዎች ላይ የማያቋርጥ ሳል ሊያስከትል ይችላል፣ ሆኖምግን በፐርቱሲስ የተያዙ ሕፃናቶች በአብዛኛው መሳል አይችሉም፣ ከመመገብ ጋር ችግር ይኖራቸዎል፣ መተንፈስ ሊያቆሙይችላሉ እና ወደ ሰማያዊነት ይለወጣሉ።

## እራስዎን እና አዲሱን ልጅዎን ለመጠበቅ በእርግዝና ወቅት ፐርቱሲስ (Tdap) ክትባት ያግኙ

- **የዩ ኤስ የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል አማካሪ ኮሚቴ ነፍሰ ጡር በእያንዳንዱ እርግዝና ወቅት በተለይም ከጽንስ ከ27 እስከ 36 ሳምንታት ባሉት ጊዜያት ውስጥ የ Tdap ክትባት እንድትወስድ ይመክራል። ይህ እርስዎን እና ልጅዎን ከፐርቱቲስ በሽታ ለመከላከል ክትባቱ የተሻለ የሚሰራበት ወቅት ነው።**
- Tdap ክትባት በእርግዝና ወቅት አስተማማኝ ነው። Tdap በእርግዝና ወቅት ከተቀበሉ፣ እርስዎ እና አዲሱ ልጅዎ በሚወልዱበት ጊዜ ከፐርቱሲስ የመጠበቅ አዝማሚያዎ የበለጠ ነው።
- ከክትባቱ የሚያገኙት የኢንፌክሽን ተዋጊ አንቲቦዲዎች ለተጨማሪ መከላከል ወደ ልጅዎ ይተላለፋሉ።
- ከነፍሰጡርነትዎ በፊት ወይም ወቅት የ Tdap ማደሻ ካላገኙ፣ ልክ ከወለዱ በኋላ እና እያጠቡ ከሆነ ምክትባቱን ማግኘት አስተማማኝ ነው።

## እርስዎ፣ ቤተሰብዎ፣ የልጅዎ ተንከባካቢዎች የፐርቱሲስ ማደሻ ያስፈልጋቸዎል

- በፐርቱሲስ የተያዙ ከአራት ሕፃናት ሦስቱ በሽታውየተጠቁ ነገር ግን እንዳለባቸውየማያውቁ ከወላጆቻቸው፣ ሌሎች የቤተሰብ አባላት፣ ወይምከተንከባካቢዎች ያገኙታል።
- ሕፃናት ቢያንስ ቢያንስ የ ስድስት ሳምንት ዕድሜእስኪሞላቸውድረስ የመጀመሪያውን የፐርቱሲስ ክትባት (DTaP) ጠብታ ማግኘት አይችሉም። በስድስተኛ ወር ዕድሜቢያንስ ቢያንስ ሦስት የ DTaP ጠብታዎች እስ ከምታገኝድረስ፣ አነስተኛ መከላከል ይኖራታል።
- ቢያንስ ቢያንስ ሦስት የ DTaP ጠብታዎች ከማግኘቱ በፊት አዲስ የወለዱትን ሕፃን ከፐርቱሲስ ለመከላከል ምርጡመንገድ እርስዎ እና ከልጅዎ ጋር ሊኖረውየሚችል እያንዳንዱ ሰው የጎረምሳ/የአዋቂ ፐርቱሲስ ማደሻ **(Tdap)** ጨምሮ፣ በፐርቱሲስ ክትባታቸውላይ ጊዜውን ጋር ሲጓዙ ብቻ ነው።

## ከዶክተርዎ፣ ነርስዎ፣ ወይምክሊኒክዎ ጋር ተወያዩ

- በነፍሰጡርነትዎ ወቅት የፐርቱሲስ ማደሻ እንዲሰጥዎ ዶክተርዎን ወይምነርስዎን ይጠይቁ። ዶክተርዎ፣ ነርስዎ፣ ወይምክሊኒክዎ ክትባቱን የማያቀርቡ ከሆነ፤ የአካባቢውመድሐኒት ቤቶች ላይ ይፈልጉ።
- ለተጨማሪ መከላከል፣ ልጅ ከመወለዱ በፊት የቤተሰብዎን አባላት ክትባት እንዲሰጡዶክተርዎን ወይምነርስዎን ይጠይቁ።



### ስለ ፐርቱሲስ ለተጨማሪ መረጃ፦

- http://www.kingcounty.gov/healthservices/health/communicable/diseases/whoopingcough.aspx
- http://www.doh.wa.gov/YouandYourFamily/IllnessandDisease/WhoopingCough.asp
- http://www.cdc.gov/features/pertussis/
- የሕዝብ ጤና ጥበቃ –ሲያትል እና ኪንግ ኮውንቲ, **206-296-4774**

ተለዋጭ ቅርፀቶች ይገኛሉ
TTY Relay: 711
206-296-4774 (ድምፅ)

Public Health
Seattle & King County